COMMENT

# የሕፃናትን ጥቅም እና ደህንነት ከማስጠበቅ አኳያ የፍርድ ቤቶች ሚና

አብርሃ መሠለ* እና መኮንን ንጉሤ**

**DOI** http://dx.doi.org/10.4314/mlr.v13i1.8

**Title:** The role of courts in safeguarding the best interest of the child


## Summary

The best interest of the child is a multifaceted principle governing children's rights. This principle is tri-dimensional which serves as (i) human right, (ii) a mechanism of evaluation of other rights, and (iii) as a means of interpreting other rights under the Convention on the Rights of the Child (CRC). Ethiopia has ratified the CRC. As the judiciary is the ultimate guardian of human rights including the rights of children, allowing the judiciary to safeguard such rights – when it adjudicates cases that affect the interest of children– is one of the mechanisms of implementing the right. Pursuant to Article 13(1) of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Constitution, the Judiciary, among others, is legally entrusted with the function of enforcing and respecting human rights. This comment explores the law relating to the interpretation and application of the best interest of the child in Ethiopia. Primary and secondary data sources indicate that there is no clear assessment and criteria-specific procedure on the use and evaluation of the best interest of the child. Consequently, there is no uniform interpretation and application of the best interest of the child by courts.



## አህጽሮተ-ይዘት

የሕፃናትን መብት እና ደህንነት ማስጠበቅ ከማናቸውም መብቶች በተለየ ሊተገበር የሚገባው ዐብይ ጉዳይ ነው፡፡ ይህም የሆነበት ዋና ምክንያት ሕፃናት ከሌሎች የሕብረተሰብ ክፍሎች በተለየ ሁኔታ ለተለያዩ የመብት ጥሰቶች የተጋለጡ በመሆናቸው ነው፡፡ ስለሆነም ሕፃናትን የሚመለከቱ ማናቸውም ዓይነት ውሳኔዎች ሲሰጡ የሕፃናት ጥቅም እና ደህንነት ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል፡፡ በተለይም የመብቶች ሁሉ ዘብ ጠባቂ በመሆን ፍትሕን የማስተዳደር ዐብይ ሥልጣን በተሰጣቸው ፍርድ ቤቶች ሕፃናትን የሚመለከቱ ውሳኔዎች ሲሰጡ ለሕፃናት ጥቅም እና ደህንነት ቅድሚያ በመስጠት ሕገ መንግሥታዊ ኃላፊነታቸውን እና ግዴታቸውን መወጣት ይጠበቅባቸዋል፡፡ የተለያዩ ሕጎችና ልምዶችን በማጣቀስ የሕፃናትን ጥቅምና ደህንነት መርህ በመጠበቅና በመፈጸም ረገድ የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ካላቸው ሚና አኳያ የተመረጡ የፍርድ ቤቶችን ውሳኔ ይህ ጽሁፍ በአጭሩ ይዳስሳል፡፡


**መሪ ቃላት:** የሕፃናት ጥቅምና ደህንነት፣ የሕፃናት መብቶች ፣ ፍርድ ቤቶች፣ ኢትዮጵያ


* አብርሃ መሠለ፡- ኤል ኤል ቢ. መቐለ ዩኒቨርሲቲ፣ ኤል ኤል ኤም አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ረዳት ፕሮፌሰር፣ መቐለ የኒቨርሲቲ፣ ሕግ ትምህርት ቤት፤ Email: expansion97@gmail.com

** መኮንን ንጉሤ፡- ኤል ኤል ቢ. ሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ፣ ኤል ኤል ኤም ደቡብ አፍሪካ የኒቨርሲቲ፣ረዳት ፕሮፌሰር፣ደብረ ማርቆስ የኒቨርሲቲ፣ ሕግ ትምህርት ቤት፤ Email: taemeretsion@gmail.com

## መግቢያ

ሕፃናት እንደማንኛውም ተፈጥሮአዊ ሰው መብት ያላቸው ቢሆኑም በሥነ-አዕምሮአዊ፣ ሥነ-ልቦናዊ፣ ማኅበራዊ ግንኙነት እንዲሁም አካላዊ ሁኔታ ምክንያት ተጨማሪ ጥበቃ እንደሚያስፈልጋቸው ዓለም አቀፍ ፣ አህጉር አቀፍ እና በአገር ደረጃ የተቀረፁ ሕጎች ደንግገዋል፡፡ ምንም እንኳ እነዚህ ሕጎች ተጨማሪ መብቶችን ለሕፃናት ቢሰጡም ተግባራዊነታቸውን በሚመለከት ወጥነት የሌለው የመርሁ አተረጓጎምና አጠቃቀም ይታያል፡፡ ዓለም አቀፍ እንዲሁም አገር አቀፍ ሕጎች የሕፃናት መብቶችን ተግባራዊ ለማድረግ እንዲቻል በማሰብ የተለያዩ መርሆዎችን ደንግገዋል፡፡ እነዚህ መርሆዎች ደግሞ ለሌሎች የሕፃናት መብቶች መከበር/ማስተግበር ከፍተኛ አስተዋፅዖ አላቸው፡፡ ከእነዚህ መርሆዎች ዋነኛው የሆነው *ለሕፃናት ጥቅምና ደህንነት ቅድሚያ መስጠት* (Best interest of the child) የሚለው መርህ ነው፡፡ በዚህም መሠረት፣ ሕፃናት ነክ ውሳኔዎች ሲወሰኑ ውሳኔ ሰጭ አካላት ለሕፃናት ጥቅምና ደህንነት ቅድሚያ በመስጠት የሕግ ግዴታቸውን መወጣት ይጠበቅባቸዋል፡፡

ይህ ጽሁፍ የመርሁን ይዘት እንዲሁም ከሌሎች የሕፃናት መብቶች ጋር ያለውን ግንኙነት ይዳስሳል፡፡ በተጨማሪም ፍርድ ቤቶች ለዚህ መርህ መፈፀም እንዲሁም ከሌሎች መብቶች ጋር ያለውን መስተጋብር በምን ያክል እንደተረዱትና እንደሚጠቀሙበት በአጭሩ እንመለከታለን፡፡ ጽሁፉ ይህን መርህ የሚዳስሰው በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን፣ በአፍሪካ ቻርተር የሕፃናት መብት እና ደህንነት፤ እንዲሁም በኢትዮጵያ ሕጎች መሠረት ነው፡፡

## 1. የ'ሕፃን' ትርጓሜ

ሕፃን ማን ነው? ለሚለው ጥያቄ የተለያዩ አገራት ሕጎች የተለያየ ትርጓሜ ሰጥተዋል፡፡ ለሕፃንነት የሕግ ትርጓሜ መስጠትን አስፈላጊ ካደረጉት ምክንያቶች መካከል ዋነኛው የመብትና ግዴታ ክልል ወሰን (scope of rights and duties) ለማወቅ ስለሚያስችል ነው፡፡ ሌላው ምክንያት ደግሞ ሕፃናት ለአደጋ ተጋላጭ ከመሆናቸው አኳያ ልዩ ጥበቃ (special protection due to vulnerability) ስለሚያስፈልጋቸው ነው፡፡

ምንም እንኳ አንድ ወጥ የሆነ የሕፃን ትርጓሜ ባይኖርም ሕፃን የሚለው ቃል ብዙ አገራት ዕድሜን ግምት ውስጥ ያስገባ ትርጉም ይጠቀማሉ፡፡[1] ከዚህም ባሻገር በአንዳንድ አገሮች ሕፃን ለሚለው ትርጓሜ ለመስጠት ማኅበራዊ አረዳድን (social construction of age) ግምት ውስጥ ያስገባሉ፣ ለምሳሌ በጉርምስና ወቅት የሚታዩ አካላዊ ለውጦች እና የድምፅ መጎርነን ከግምት ውስጥ ይገባሉ፡፡[2]

በዓለም አቀፍ የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን አንቀፅ 1 የተመለከተው ዕድሜን መሠረት ያደረገ ትርጉም ሲሆን፣ "ሕፃን ማለት ማንኛውም ዕድሜው ከአሥራ ስምንት ዓመት በታች የሆነ የተፈጥሮ ሰው"[3] እንደሆነ ይገልፃል፡፡ ሆኖም፣ አገራት በሚያወጡት ሕግ መሠረት ከአሥራ ስምንት ዓመት በታች መውረድ የሚቻልበት አጋጣሚም እንዳለ በኮንቬንሽኑ ተገልጧል፡፡ ይህ በሚሆንበት ጊዜ ሕፃኑ ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ እንደወጣ (emancipated) ይቆጠራል፡፡ ይህ የዕድሜ ጣራ መዳረሻ (አሥራ ስምንት ዓመት) ከየት እንደሚጀምር በግልፅ የተደነገገ ነገር ባይኖርም በኮንቬንሽኑ መግቢያ ላይ እንደተገለፀው ከመወለድ በፊትም፣ ማለትም በጽንስ ወቅትም ጥበቃ እንዳለ እንገነዘባለን (protection may be given before birth during conception)፡፡

የአፍሪካ የሕፃናት መብቶች እና ደህንነት ቻርተር አንቀፅ 2 ሕፃን ለሚለው ትርጓሜ የሚከተለውን ደንግጓል፡-

> "ለዚህ ቻርተር ዓላማ ሲባል ሕፃን ማለት ማንኛውም ዕድሜው ከአሥራ ስምንት ዓመት በታች የሆነ የተፈጥሮ ሰው ነው፡፡"

---

[1] Don Cipriani (2009), *Children's Rights and the Minimum Age of Criminal Responsibility: A Global Perspective* (Advances in Criminology). Ashgate Publishing

[2] ዝኒ ከማሁ

[3] *Convention on the Rights of the Child,* General Assembly Resolution 44/25 of 20 November 1989 entry into force 2 September 1990

ይህ አህጉር አቀፍ የሆነ ቻርተር ከአፍሪካ ነባራዊ የሕፃናት ችግር በመነሳት የተቃኘ ነው፡፡ የሕፃን ትርጉምን በተመለከተ ቻርተሩን ያፀደቁ አገራት ከቻርተሩ በተለየ መልኩ የራሳቸው የሕፃን ትርጓሜ ሕግ እንዲኖራቸው ቻርተሩ የማይፈቅድ ሲሆን፣ በዚህ ረገድ በዓለም አቀፍ የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን ልዩነት አለው፡፡ በዚህም ምክንያት ሕፃናት አሥራ ስምንት ዓመት ሳይሞላቸው ከሞግዚት ነፃ የሚወጡበት መንገድ የለም፡፡ ሆኖም ግን ቻርተሩ እንደ ዓለም አቀፉ የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን የሕፃንን ዕድሜ ጣሪያ ከመግለፅ ባለፈ የመነሻ ዕድሜ የለውም፡፡

ወደ ኢትዮጵያ ስንመጣ ደግሞ የተለያየ የሕፃን ትርጓሜ ሊኖር የሚችልበት ዕድል ተፈጥሯል፡፡ ምክንያቱም የ1987 ዓ.ም የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራስያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት ለፌዴራላዊ ሥርዓት ዕውቅና[4] በመስጠት፣ ፌዴራል መንግሥትና ክልሎች የየራሳቸውን የቤተሰብ ሕግ እንደሚያወጡ ይፈቅዳል፡፡

በፌዴራል የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 215 መሠረት አካለ መጠን ያልደረሰ ሰው ማለት ጾታ ሳይለይ ዕድሜው አሥራ ስምንት ዓመት ያልሞላው ልጅ ነው፡፡[5] ይህ የዕድሜ መነሻ በዚህ ሕግ በግልፅ ባይቀመጥም በ1952 ዓ.ም በወጣው የፍትሐብሔር ሕግ አንቀፅ 1 እና 2 ከመወለድ በፊት ገና ለተፀነሰ ልጅ ጥበቃ ተደርጓል፡፡ ነገር ግን ሕፃኑ ሲወለድ በሕይወት መወለድ እንዳለበትና ቢያንስ ለ48 ሰዓት በሕይወት ሊቆይ የሚችል (viable) ሊሆን እንደሚገባ በፍትሐ-ብሔር ሕግ በአንቀጽ 2 እና 4 ተደንግጓል፡፡

## 2. ሕፃናት ሌሎች ሰዎች ከሚደረገው ተጨማሪ ጥበቃ ለምን አስፈለጋቸው?

ሕፃናት በአእምሮአቸው፣ በአካላቸውና በሥነ- ልቦናቸው ያልበሰሉ፣ የማመዛዘንና ተገቢና ጠቃሚ ውሳኔ የማስተላለፍ አቅም የሌላቸው የሕብረተሰብ ክፍሎች ናቸው፡፡ በዚህም የተነሳ ለተለያዩ ችግሮች በቀላሉ ተጋላጭ የመሆን ዕድላቸው የሰፋ ነው፡፡ ይህንን ተጋላጭነታቸውን ግምት ውስጥ በማስገባት፤ ሌሎች ሰዎች ካላቸው ጥበቃ ባሻገር ተጨማሪ ጥበቃዎችና ከለላዎችን መስጠት አስፈላጊና አስገዳጅ ሆኗል፡፡

የሰብአዊ መብቶች ሕግ ለሰው ልጆች ጥበቃ ሲባል ምንም እንኳ በቅርቡ የዳበረ ሕግ ቢሆንም፤ ሰዎች በተፈጥሮ ሕግጋት የተሰጧቸው መብቶች አሏቸው፡፡[6] የሕፃናት መብቶች ሕግም ከሌሎች ሰዎች መብቶች ሕግ ባልተለየ ሁኔታ በ20ኛው ግማሽ ክፍለ ዘመን ዕውቅና እንዳገኘ የሕግ ምሁራን ያስረዳሉ፡፡[7] ሆኖም ሕፃናት ለብዙ ዓመታት መብቶቻቸው ሳይከበሩላቸው መቆየታቸውን የሰብአዊ መብቶች የታሪክ ምሁራን ያስቀምጣሉ፡፡[8]

አንደኛውና ሁለተኛው የዓለም ጦርነቶች በሕፃናት ላይ ያስከተሉትን ዘርፈ-ብዙ ሰቆቃና ኢ-ሰብአዊ ድርጊት ከግምት ውስጥ በማስገባት እኤአ በ1989 የተፈረመው የተባበሩት መንግሥታት የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን ሕፃናት የመብት ባለቤት መሆናቸውን ደንግጓል፡፡[9] የሕፃናትን የመብት ባለቤትነት በተመለከተ የተለያዩ ንድፈ-ሐሳባዊ አስተያየቶች (ቲዮሪዎች)[10] ቢኖሩም ዋና ዋናዎቹ[11] የሚከተሉት ናቸው፡፡

[4] የኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት አንቀፅ 1 እና አንቀፅ 50(1) ይመለከተዋል፡፡

[5] ለምሳሌ የኦሮሚያ ክልል የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 69/1995 በአንቀጽ ቁጥር 232 አካለ መጠን ያልደረሰ ሰው ማለት ጾታ ሳይለይ ዕድሜው አሥራ ስምነት ዓመት ያልሞላው ሰው ነው፡፡

[6] John Tasioulas (2015). On the Foundations of Human Rights, in Philosophical Foundations of Humuan Rights

[7] James Griffin (2008), *On Human Rights*. Oxford Universit Presss

[8] A. Glenn Mower, Jr. (1997), *The Convention on the Rights of the Child.* International Law Support for Children, Greenwood press, London. Studies in Human Rights, Number 17, page 11

[9] Article 12(1) of the UN Convention on the Rights of the Child, UN General Assembly 44/25 of20 November 1989

[10] Louise Ehlers and Cheryl Frank (2008), *Child Participation in Africa* in Julia Sloth-Nielsen (2008) Children's Rights in Africa. University of the Western Cape

[11] ዝኒ ከማሁ

### 2.1 ዌልፌር ቲዮሪ (Welfare Theory)

ሕፃናት ሥነ-አመክንዮአቸው (reasonableness and rationality) ያልበሰለ፣ አዕምሯቸው ያልበለፀገና በአዋቂዎች ላይ ጥገኛ የሆኑ፣ ለራሳቸው የሚያስፈልጋቸውን ነገር በተመለከተ በአቅመ አዳም/ሔዋን ያሉ ቤተሰቦቻቸው እየወሰኑላቸው የሚኖሩ ናቸው የሚል ቲዎሪ ነው፡፡[12] ይህ ቲዎሪ ሕፃናት ያልተፃፈባቸው ነጭ ወረቀት እንደሆኑ አድርጎ የሚያስብና በአዋቂ ሰዎች ዕውቀት የሚመሩ፣ የሚተዳደሩ በመሆኑ ጥበቃ ያስፈልጋቸዋል የሚል ነው፡፡ ይህም ሕፃናት በራሳቸው ጉዳይ ምንም ዓይነት ተሳትፎ እንዳይኖራቸው ከማድረጉም ባሻገር የሕይወት ልምድ እንዳይቀስሙና እንዳያዳብሩ አድርጔል፡፡ በመሆኑም ሕፃናት ከለላና ድጋፍ ብቻ እንደሚያስፈልጋቸው የሚያቀንቅን ቲዎሪ ነው፡፡ ይህ ቲዎሪ የሕፃናትን ዕድሜ እና የብስለት ደረጃ ከግምት ውስጥ ሳያስገባ ሕፃናት በቤተሰቦቻቸው ቁጥጥር ውስጥ እንዲሆኑ የሚያደርግ ነው፡፡[13]

### 2.2 ሊብራል ቲዮሪ (Autonomous Theory)

ሕፃናት ለብዙ ዓመታት የቤተሰቦቻቸው ንብረት ሆነው በራሳቸው ጉዳይ ምንም ዓይነት ተሳትፎ እንዳይኖራቸው ተደርጓል የሚል ቲዮሪ ነው፡፡[14] ይህ ቲዮሪ ይህንን ጭቆና ለመዋጋት ሕፃናት በራሳቸው ጉዳይ መሳተፍ አለባቸው ብሎ ያምናል፡፡ በራሳቸው ጉዳይ ላይ መሳተፋቸው (እየተሳሳቱም ቢሆን) የሕይወት ልምድ ያስገኝላቸዋል፡፡ በመሆኑም ሕፃናት ያለ ምንም ገደብ በራሳቸው ጉዳይ ላይ እንዲሳተፉ የሚፈቅድ ሀልዮት (ቲዮሪ) ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ቲዮሪ ሕፃናት ከዕድሜያቸው ለጋነት እና ከአዕምሮአቸው የብስለት ውስንነት አኳያ ያለባቸውን ተጋላጭነት ከግምት ውስጥ ያላስገባ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡[15] ምክንያቱም፣ ከመወለድ አንስቶ እስከ አሥራ ስምንት ዓመት ባለው የዕድሜ ዘመን ሕፃናት እንደ ዕድሜያቸው በእናት እና አባቶቻቸው አማካይነት የሚጠበቁበትና ነፃነት የሚያገኙበት ሚዛን እንደ ዕድሜያቸው መጠን የሚለያይ ነው፡፡

## 3. የሕፃናትን ጥቅምና ደህንነት የማስጠበቅ መርህ አጠቃላይ ጽንስ ሓሳቦችና የሕፃናት ጥቅምና ደህንነት አወሳሰን

የሕፃናትን ጥቅምና ደህንነት ሊጎዱ የሚችሉ ሁኔታዎች በጥቂቱም ቢሆን በሕግ ተደንግገው ይገኛሉ፡፡ ለምሳሌ ዘረ-መል (genetic)፣ ገንዘብ ነክ፣ ትምህርት፣ አካባቢ እና ዝምድናን የሚመለከቱ ጉዳዮች እንደ የአፈጻጸማቸው መልካም ወይም መጥፎ ሁኔታዎችን በሕፃናት ላይ ይፈጥራሉ፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች (factors) በአንድ ላይ ተደማምረው የልጆችን መልካም ዕድገት (welfare of children) ያመጣሉ ተብሎ ይታሰባል፡፡[16]

የሕፃናት ጥቅምና ደህንነት መርህን[17] በመከተል ፍርድ ቤቶች የሕፃናት ጉዳይ ላይ ሲወስኑ ከሕፃናት ጥቅምና ደህንነት አንጻር መወሰን እንዳለባቸውና ይህንን ጥቅም ወይም ግልጋሎት ማን በበለጠ ለሕፃናቱ መስጠት እንደሚችል ግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው፡፡[18] ሕፃኑ ምን ዓይነት አገልግሎት፣ ትኩረትና ክብካቤ እንደሚያስፈልገው በማጤን ከሕፃኑ *ጥቅምና ደህንነት* አኳያ ከማን ጋር ቢያድግ ለመልካም ዕድገቱ እና ትምህርቱ አመቺ እንደሚሆን በመወሰን ሂደት የሕፃናት ጥቅምና ደህንነት መርህን [19] መከተል ያስፈልጋል፡፡

---

[12] Deirdre Fottrell. (2000), *Revisiting Children's Rights: 10 Years of the UN Convention on the Rights of the Child*. Kluwer Law International, The Hague.
[13] ዝኒ ከማሁ
[14] ዝኒ ከማሁ
[15] ዝኒ ከማሁ
[16] UNHCR Guidelines on Determining the Best Interest of the Child (2008)
[17] የሕፃናት ጥቅምና ደሕንነት መርህ ከአራቱ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሕፃናት መብት ኮንቬንሽን ዋና ዋና መርሆዎች ማለትም በሕጻናት መካከል አድልዎ አለማድረግ(non-discrimination clause)፣ የሕፃናት በሕይወት የመኖር ፣ጤናማ እና መልካም እድገት(the right to life, survival and development) እንዲሁም የሕፃናት ተሳትፎ(the right to particiaption) መርህ አንዱ ነው፡፡
[18] UNHCR Guidelines on Determining the Best Interest of the Child (2008)
[19] ዝኒ ከማሁ

የሕፃናት ጥቅምና ደህንነት አወሳሰን ስንል ጥቅሞቻቸውንና ደህንነታቸውን የሚነዱ በተለይ ጠቃሚ ውሳኔዎችን ለመወሰን በሚያስችል በጥብቅ ሥነ-ስርዓት የሚተገበር መደበኛ ሂደት ማለታችን ነው። የሕፃናትን በቂ ተሳትፎና ተሰሚነት ማረጋገጥና ማበረታታት ለሕፃናት ጥቅምና ደህንነት ጥበቃ የላቀ አስተዋፅኦ አለው። ከዚህ ባለፈ የተለያዩ ባለሙያዎችና ከፍሬ ነገሩ ጋር ተያያዥነት ያላቸው እንዲሳተፉ ማድረግ ተገቢ ነው።

### 3.1 የሕፃናትን ጥቅምና ደህንነት ለመወሰን የሚረዱ ነጥቦች[20]

የሕፃናትን ጥቅምና ደህንነት በመወሰን ሂደት የሚከተሉት ፍሬ-ሓሳቦች ግምት ውስጥ መግባት አለባቸው።

**ሀ) የቤተሰብ አብሮነትና ቤተሰባዊ ድባብ** (Family integrity and environment) **የሚሰጠው ጥቅምን ግምት ውስጥ ማስገባት**

አንድ ሕፃን ከቤተሰብ ጋር አብሮ በሚኖርበት ጊዜ የማንነት መገለጫ እንዲሁም ሥነ-ልቦናዊ ጤንነት የሆኑትን እንደ የቤተሰብ ፍቅር፣ ባህልና ወግ፣ ቋንቋ ወዘተ ያገኛል። እነዚህ የቤተሰብ አብሮነት ትሩፋቶች በሕፃኑ የመልካም አስተዳደግ ሁኔታ ውስጥ ትልቅ ፋይዳ አላቸው። ስለሆነም ማናቸውም ሕፃናትን የሚመለከቱ ውሳኔዎች ሲወሰኑ ውሳኔውን የሚያሳልፈው አካል (በተለይ ፍርድ ቤቶች) የቤተሰብ አብሮነት የሚሰጠውን ጥቅም ከግምት ውስጥ ማስገባት ይገባቸዋል።[21]

**ለ) የልጁን መልካም ጤንነት፣ ደህንነትንና ጥበቃ ግምት ውስጥ ማስገባት**

ይህ መስፈርት ሕፃናት በተለያየ ምክንያት የቤተሰብ መለያየት ሲያጋጥማቸው የትና ከማን ጋር ይደጉ? ለሚለው መሠረታዊ ጥያቄ ምላሽ የሚሰጥ ነው። ለምሳሌ በፍቺ፣ በሞትና በመጥፋት ወዘተ... የቤተሰብ መፍርስ ሲያጋጥም ፍርድ ቤቶችም ሆኑ ሌሎች የሕፃናቱ ጉዳይ የቀረበላቸው ውሳኔ ሰጭ አካላት ሕፃናቱ የት ቢያድጉ ለመልካም አስተዳደጋቸው እንዲሁም ደህንነትና ጥበቃ የተሻለ ይሆናል የሚለውን መስፈርት ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል። ሕፃናቱ ከአባታቸውና ከእናታቸው ሲለዩ ለመልካም ዕድገታቸው፣ ትምህርታቸው፣ መልካም ጥበቃና እንክብካቤ እንደሚደረግላቸው ውሳኔ ሰጭ አካላት ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል።[22]

**ሐ) ወቅቱን የጠበቀና የማይለዋወጥ ውሳኔ ማሳለፍ**

ይህ ፍሬ-ሓሳብ የሚያመለክተው ሕፃናት ተጋላጭ የሕብረተሰብ ክፍሎች ከመሆናቸው የተነሳ ጥቅማቸውን የተመለከተ ውሳኔ ሲሰጥ ጉዳያቸው በወቅቱና መፍትሔ ሊያመጣ በሚችል አኳኋን መወሰን እንደሚገባው ነው። ውሳኔው በዘገየና በተንተተ ቁጥር 'በዕንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ' እንዲሉ የሕፃናት ተጋላጭነት እየተባባሰና እየገዘፈ ለከፋ እንግልትና የመብት ጥሰት ይዳርጋቸዋል። ይህ እንዳይሆን ውሳኔ ሰጭ አካላት የሕፃናቱን ጥቅምና ደህንነት በተመለከተ ወቅቱን በጠበቀና መፍትሔ ሊሰጥ በሚችል አኳኋን ውሳኔ መስጠት አለባቸው።[23]

**መ) የልጁን አስተያየትና ሓሳብ በአግባቡ መስማትና ተገቢውን አፅንኦት መስጠት**[24]

የሕፃናቱን ጥቅምና ደህንነት የሚመለከቱ ጉዳዮች በሚወሰኑበት ወቅት ፍርድ ቤቶችም ሆኑ ሌሎች ውሳኔ ሰጭ አካላት ውሳኔ ከማሳለፋቸው በፊት ጠቃሚ ይሆናል በሚሉት አግባብ የሕፃናትን አስተያየትና ሓሳብ በአግባቡ መስማትና ተገቢውን አፅንኦት መስጠት ይገባቸዋል። ሆኖም ግን ይህ የሚሆነው ሕፃናቱ አስተያየት ለመስጠት የሚያስችላቸው የዕድሜ ደረጃ እና ብስለት ላይ ሲሆኑ

---

[20] ዝኒ ከማሁ

[21] ዝኒ ከማሁ

[22] ዝኒ ከማሁ (Assure that the child when removed will be given due care, treatment and guidance which promote his/her overall development).

[23] ዝኒ ከማሁ

[24] (Providing the child with participatory opportunity when the child can make valid opinions) Michael Freeman (2007), *A Commentary on the United Nations Convention on the Rights of the Child*. University College London, Martinus Nijhoff publisher.

ነው፡፡ ለምሳሌ በፊንላንድ ሕግ መሠረት ሕፃኑ ከ12 ዓመት ዕድሜ በላይ ሲሆን አስተያየቱን በመስጠትና የውሳኔ አካል በመሆን በውሳኔ ላይ ይሳተፋል፡፡[25]

**ሠ) የአሁኑን እና የወደፊቱን የሕፃናት ጥቅምና ደህንነት ሚዛን መጠበቅ** (Striking the balance between the current interest and future interest of the child)

የሕፃናቱን ጥቅምና ደህንነት በሚመለከት ጉዳይ ዳኞች ውሳኔ ሲሰጡ የሕፃናቱን የአሁንና የወደፊቱን ሁኔታ በማገናዘብ ውሳኔ ማሳለፍ እንዳለባቸው ይህ ጽንስ-ሓሳብ ያስገነዝባል፡፡ ማለትም፣ የሕፃናቱን ወቅታዊ የዕድሜና ሌሎች ነባራዊ ሁኔታዎች (current interests) ከወደፊት ሁኔታዎች (future interest) አንፃር በማገናዘብ ዳኞች ውሳኔ መስጠት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ለምሳሌ ውሳኔ በሚሰጥበት ወቅት የሕፃኑ ዕድሜ 13 ቢሆን ዳኞች ይህ ሕፃን በ13^ኛው ዓመቱ ምን ያስደስተዋል የሚለውን እንደ ወቅታዊ (current) ጥቅሞች በመመዘን እና ይኸው ውሳኔ ለሕፃኑ የጎልማሳነት ሕይወት የሚያስከትለውን ጥቅም ጭምር በማመዛዘን ውሳኔ ማሳለፍ አለባቸው፡፡ ውሳኔ ሰጭ አካላት ጥንቃቄ በተሞላበት ዘዴ ይህን ጉዳይ ካላከናወኑት የሕፃናትን ጥቅምና ደህንነት የማስጠበቅ ዓላማ ለማሳካት አስቸጋሪ ነው፡፡[26]

### 3.2 የሕፃናት ጥቅምና ደህንነት መርህ ግምገማ

የአንድን ሕፃን ጥቅምና ደህንነት ከግምት ውስጥ ያስገባ ውሳኔ መሰጠቱ የሚገመገመው በባለሙያዎች ስብስብ ነው፡፡ አንዳንድ አንኳር ውሳኔዎች ከመወሰዳቸው በፊት የሕፃናትን ጥቅምና ደህንነት ለመለየት ሁሌም ጥብቅ የሥነ-ሥርዓት ጥበቃዎች (strict procedural safeguards) በብሔራዊ የሕፃናት ጥበቃ ሥርዓት ውስጥ ይካተታሉ፡፡ ይህም ከሕፃኑ ፈቃድ ውጭ ከቤተሰብ መለየትን፣ ጉዲፈቻና የቤተሰብና የሕፃናት ጥበቃ መብቶችን (parental and custody rights) ለመወሰን ያገለግላል፡፡[27] እነዚህ ውሳኔዎች ሊወሰዱ የሚችሉት በሚመለከታቸው አካላት (ለምሳሌ በፍርድ ቤቶች) ሲሆን በሕግ የተደነገጉ የሥነ-ሥርዓት ከለላዎችን (procedural safeguards) መሠረት ያደረጉ መሆን አለባቸው፡፡

## 4. በሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን መሠረት ለሕፃናት ጥቅምና ደህንነት ቅድሚያ ስለመስጠት

እስከ እ.ኤ.አ.1980ዎቹ ሁሉን አቀፍና አስገዳጅ የሆነ የሕፃናት መብቶች ሕግ በዓለም አቀፍ ደረጃ ባይኖርም ሕፃናትን የሚመለከቱ አንዳንድ ድንጋጌዎች በተለያዩ ጥራዞች ተሰባጥረው ይገኙ ነበር፡፡ ለምሣሌ እ.ኤ.አ በ1973 በቁጥር 138 በወጣው አይ ኤል ኦ ኮንቬንሽን (ILO Convention Number 138)፤ በ1949 እ.ኤ.አ የሲቪል ሰዎችን ጥበቃ ለማድረግ በወጣው የአራተኛው ጄኔቫ ኮንቬንሽን (the 1949 IV Geneva Convention on the Protection of Civilians during Wartime)፤ በ1959 እ.ኤ.አ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሕፃናት መብቶች መግለጫ እና በተለያዩ ፕሮቶኮሎች ወዘተ… የሕፃናት መብቶች ተካተዋል፡፡

በሁለቱ የዓለም ጦርነቶች ወቅት ሕፃናት ከማናቸውም የሕብረተሰብ ክፍሎች በተለየ ሁኔታ ግፍና ሰቆቃ ደርሶባቸዋል፡፡ ለምሳሌ እ.ኤ.አ በ1980ዎቹ በተደረገው የዳሰሳ ጥናት እንደተገለፀው፡-[28]

- 100 ሚሊዮን የሚሆኑ ቤተሰብ አልባ ሕፃናት ለተለያዩ ከባድ የጉልበት ሥራ፣ ሴተኛ አዳሪነት ተግባር፣ ለወንጀል እና ልመና ተዳርገዋል፤
- 50 ሚሊዮን የሚሆኑ ሕፃናት ጤንነቱ ባልተጠበቀና አደገኛ በሆነ የሥራ ሁኔታ ውስጥ ሁነው እንዲሠሩ ተገደዋል፤
- ዕድሜያቸው ከ 6-11 የሚሆኑ 120 ሚሊዮን ሕፃናት ትምህርት ቤት አልገቡም፤
- በየዓመቱ 3.5 ሚሊዮን ሕፃናት መከላከል በሚቻሉና ሊድኑ በሚችሉ በሽታዎች ለሞት ተዳርገዋል፤

---

[25] *K and T* v. *Finland* [2001] 2 FLR 707. In Michael Freeman (2007). *A Commentary on the UN Convention on the Right of the Child*, Martinus Nijhoff Publisher, page 31

[26] UNHCR Guidelines on Determining the Best Interest of the Child (2008)

[27] ዝኒ ከማሁ

[28] A. Glenn Mower, Jr. (1997), *supra* note 8

- ዕድሜያቸው ከአምስት ዓመት በታች የሆኑ 155 ሚሊዮን ሕፃናት በከፋ ድህነት ውስጥ እንዲኖሩ ሆነዋል፤
- በአደጉ አገራትም ጭምር በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሕፃናት ለፆታዊ ትንኮሳ፣ ለአደንዛዥ ዕፅ እና ለአላስፈላጊ እንግልትና መገለል ተዳርገዋል፡፡[29]

ከእነዚህ ችግሮች አኳያ፣ ሕፃናት ከየትኛውም ጊዜ በበለጠ ተጨማሪ ጥበቃ እንደሚያስፈልጋቸው በመገንዘብ፣ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ሰፋ ያለ የሕግ ማዕቀፍ ማለትም የተባበሩት መንግሥታት የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን እኤአ በ1989 አውጥቷል፡፡ ይህን የሕግ ማዕቀፍ ኢትዮጵያ እኤአ ዲሴምበር 9 ቀን 1991 ያፀደቀችው ሲሆን፣ በክፍል 4.1 ዘርዘር አድርገን እናየዋለን፡፡

የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን እ.ኤ.አ በ1989 ይፋ የተደረገ ሲሆን እ.ኤ.አ በ1990 በአባል አገራቱ ፀድቆ ወደ ሥራ ገብቷል፡፡ ከዚህ ቀደም ከነበሩት የሕፃናት መብቶች ማስጠበቂያ ድንጋጌዎች በላቀ ሁኔታ ይህ ኮንቬንሽን በተደራጀና ግልፅ በሆነ መልኩ የሕፃናት መብቶችን ደንግጓል፡፡ ኮንቬንሽኑ ሕፃናትን የተለያዩ መብቶች ባለቤት ከማድረጉም በላይ የሕፃናት መብቶች ተዘርዝረው እና ግልፅ ሆነው በዓይነትም ሆነ በስፋት ተሻሽለው እንዲደነገጉ ረድቷል፡፡ እኤአ በ1995 ብትፈርምም፣ እስከዛሬ ድረስ ኮንቬንሽኑን ካላፀደቀችው ከዩናይትድ ስቴትስ በስተቀር ሁሉም የዓለም አገራት ኮንቬንሽኑን የሕጋቸው አካል አድርገውታል፡፡[30] ይህም የሚያሳየው የሕፃናት መብትና ጥቅም ጥበቃ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ትኩረት ያገኘ መሆኑን ነው፡፡

### 4.1 የተባበሩት መንግሥታት የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን ጠቀሜታ

ይህ ኮንቬንሽን ከላይ ከተጠቀሱት ጥቅሞች በተጨማሪ ከሕፃናት መብት እና ጥቅም መጠበቅ አኳያ ብዙ አዳዲስ ነገሮችን ይዞ መጥቷል፡፡ እነዚህም የሚከተሉት ናቸው፡፡[31]

ሀ) ከዚህ ቀደም ካሉት የሕፃናት መብት ድንጋጌዎች በተለየ መልኩ ይህ ኮንቬንሽን ሕፃናት የመብት ባለቤት እንዲሆኑ በማስቻል ሰፊ አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡

ለ) ኮንቬንሽኑ ከዚህ በፊት ከነበሩት የሕፃናት መብት ድንጋጌዎች በተሻለ መልኩ የሕፃናት መብቶች በአድማስ እና በይዘት ልቀው እንዲደነገጉ አድርጓል፡፡ በተለያዩ ዓለም አቀፍ ሕጎች ተሰበጣጥረው የነበሩትን የሕፃናት መብቶች በአንድ ላይ በማጠቃለል እና ተጨማሪ መብቶችን በማካተት የጎላ ጠቀሜታ አበርክቷል፡፡

ሐ) የሕፃናቱን መብት እና ጥቅም ማስጠበቅ ለአገር ካለው ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ፋይዳ በተጨማሪ ለዓለም ኢኮኖሚ መጎልበትም ጭምር ያለውን አስተዋፅኦ ግምት ውስጥ በማስገባት ተጠቃሎ የተዘጋጀ የሕግ ማዕቀፍ ነው፡፡[32]

መ) ኮንቬንሽኑ በፈራሚ አገሮች ላይ ከፍተኛ አዎንታዊ ተፅእኖ ፈጥሯል፡፡ በብዙ አገራት እውቅና አግኝቶ በሕጎቻቸው ውስጥ መካተቱ ለሕፃናት መብት እና ጥቅም ጥበቃ ከፍተኛ ፋይዳ አለው፡፡ የኮንቬንሽኑ ትግበራ የሕፃናት መብትና ጥቅም ጥበቃን በሚመለከት ፈራሚ አገሮች የቅርብ ክትትል እንዲያደርጉ ያስችላቸዋል፡፡

ሠ) በአጠቃላይ ይህ ኮንቬንሽን ለሕፃናት መብት እና ጥቅም መጠበቅ ካለው ዓላማ አንፃር መብቶች እርስ በርሳቸው የተሳሰሩና የተዛመዱ የመሆናቸውን መርህ[33] በግልፅ አመላክቷል፡፡

---

[29] Center for Human Rights, The Right of the Child (Fact Sheet No. 10) (Geneva, Switzerland: United Nations, 1990), p.2. As cited in A. Glenn Mower, Ibid.

[30] እኤአ እስከ 12/3/2018 ባለው ጊዜ ውስጥ ነው፡፡

[31] ከላይ በግርጌ ቁጥር 10 ላይ የተጠቀሰውን ይመልከቱ

[32] Deirdre Fottrell. (2000).Revisiting Children's Rights: 10 Years of the UN Convention on the Rights of the Child.Kluwer Law International, The Hague.

[33] Vienna Declaration and Program of Action 1993

### 4.2 የኮንቬንሽኑ ዋና ዋና መርሆዎች

አራት ዋና ዋና መርሆዎች በሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን ውስጥ የተዘረዘሩትን ሌሎች መብቶች ለማስፈፀም እና ለመተርጎም የሚያገለግሉ ናቸው። እነርሱም፣

ሀ) የእኩልነት መብት (The Non-discrimination clause)፣ የኮንቬንሽኑ አንቀፅ 2፣

ለ) ለሕፃናት ጥቅምና ደህንነት ቅድሚያ መስጠት (The Best Interest of the Child)፣ የኮንቬንሽኑ አንቀፅ 3፣

ሐ) የመሳተፍ መብት (The Right to participation)፣ ኮንቬንሽኑ አንቀፅ 12፣ እና

መ) በሕይወት የመኖር እና የመልካም አስተዳደግ መብት (The Right to life, survival and development)፣ የኮንቬንሽኑ አንቀፅ 6፣

ናቸው።

### 4.3 ለሕፃናት ጥቅምና ደህንነት ቅድሚያ የመስጠት መርህ

ይህ መርህ ዕለት ከዕለት የሕፃናት መብትን የሚመለከቱ ውሳኔዎች በሚሰጡበት ጊዜ ተቋማት፣ በተለይም ፍርድ ቤቶች ለሕፃናት ጥቅም እና ደህንነት ቅድሚያ በመስጠት ኃላፊነታቸውንና ግዴታዎቻቸውን እንዲወጡ የሚያስገነዝብ ነው።[34] ያም ሆኖ ግን፣ የኮንቬንሽኑ አንቀፅ 3(1) ንባብ የመጨረሻ ሀረግ ማንኛውም አካል መንግሥታዊም ሆነ የግል ማበራዊ የደህንነት ተቋም ሕፃናትን የሚመለከቱ ማናቸውም እርምጃዎች ሲወስድ የሌሎች ሰዎች ጥቅም ከግምት ውስጥ የሚገባበት አጋጣሚ እንደሚኖር ያመለክታል። የሕፃናት ጥቅም እና ደህንነት ቅደሚያ የመስጠት መርህ በሌሎች ጥቅሞች ሳቢያ ሊጣስ የሚችልበት አግባብ አለ ማለት ነው። ውሳኔ ሰጭ አካላት የሕፃናትን ጉዳይ በሚወስኑበት ጊዜ ሰፊ የሆነ ፈቅደ ሥልጣን (discretion) ማግኘታቸው መርሁን የሚያጣብብ ነው[35] ። ይህ የመርሁ መጣበብ ሁኔታ የተከሰተው እ.ኤ.አ በ1959 የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሕፃናት መብቶች መግለጫ ይፋ ከሆነ በኋላ ነው። መግለጫው ለመጀመሪያ ጊዜ ለሕፃናት ጥቅም እና ደህንነት ቅድሚያ መስጠት የሚለውን መርህ አካቶ የወጣ ዓለም አቀፍ ሰነድ ነው። ነገር ግን መግለጫው ሙሉ በሙሉ የሕፃናት መብት ጉዳይ በማናቸውም ጊዜ ቢሆን ቅድሚያ መሰጠት እንዳለበት ይገልፅ ስለነበር አገራት ሌላ አማራጭ እንዲቀርብላቸው በመጠየቃቸው ምክንያት በሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን አንቀፅ 3 ንኡስ አንቀፅ አንድ ተተክቷል።

ይህ መርህ ራሱን የቻለ መብት ከመሆኑም ባሻገር ለሌሎች መብቶች የተለያየ ጠቀሜታ እንደሚሰጥ ታስቦ የተቀረፀ ነው። መርሁ በመጀመሪያ ደረጃ ለሌሎች መብቶች የትርጉም መሠረት በመሆን እንዲሁም በሥነ-ሥርዓት ደንብነት[36] በማገልገል ወሳኝ ሚና ይጫወታል።[37] ለዚሁ ማረጋገጫ የሚሆነው በኮንቬንሽኑ የተለያዩ አንቀጾች ላይ በተደጋጋሚ መገለፁ ነው።

### 4.4 በኮንቬንሽኑ ተግባራዊነት ረገድ የሚታዩ ተግዳሮቶች

ምንም እንኳን ኮንቬንሽኑ ከላይ የተዘረዘሩትን ጠቀሜታዎች ቢያስገኝም፣ ሙሉ በሙሉ ተተግብሮ የታለመለትን ውጤት እንዳያመጣ ተግዳሮቶች ተጋርጠውበታል። ከተግዳሮቶቹ መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡-

ሀ) ፈራሚ አገራት የሕፃናት መብቶችን እየመረጡ ማስፈፀማቸው (*a'la carte approach*) ዐብይ ተግዳሮት ነው። ፈራሚ አገሮች ኮንቬንሽኑ ያካተታቸውን መብቶች ሙሉ በሙሉ አፅድቀው

---

[34] "In all actions concering children, whether undertaken by public or private social welfare institutions, courts of law, administrative authorities or legislative bodies, the best interest of the child shall be a primary consideration."

[35] (It gives an opportunity for decision makers to consider other interests by neglecting the best interest of the child in extreme cases) ከላይ በግርጌ ቁጥር 9 ላይ የተጠቀሰውን ይመልከቱ

[36] General comment No. 14 (2013) on the right of the child to have his or her best interests taken as a primary consideration (art. 3, para. 1)

[37] Stephen Parker (1994) The Best Interests of the Child; Principles and Problems' 8 *International Journal of Law and the Family* 26.

ከተቀበሉ እና ለማስተግበር ቃል-ኪዳን ከገቡ በኂላ የሚፈልጉትን የመብት ዓይነት እየመረጡ በከፊል ማስተግበራቸው ይስተዋላል፡፡

ለ) ኮንቬንሽኑ በብዙ አገሮች መፈረሙ ብቻ በቂ እና ለሕፃናቱ መብት መከበር እንደዋስትና እንደሚያገለግል አድርጎ የመውሰድ ዝንባሌ (complacency approach) ይታያል፡፡ ይህም ቃል-ኪዳንን እና ተግባርን እንደ አንድ አድርጎ በመውሰድ መርካትን የሚያንፀባርቅ ነው፡፡

ሐ) ኮንቬንሽኑ በየአገራቱ ተፈርሞ ሲፀድቅ ዓለምአቀፋዊ ይዘት እና ትግበራ እንዳለው በመገንዘብ ቢሆንም፤ በተግባር ሲፈፀም ግን የየአገራቱን ባህል፣ ወግ እንዲሁም ሌሎች ነባራዊ ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት አለመተግበሩ (the dilemma between universalism and cultural pluralism) ለሕፃናት መብቶች አለመተግበር ችግር አስከትሏል፡፡

## 5. በአፍሪካ የሕፃናት መብቶችና ደህንነት ቻርተር

ምንም እንኳ የሕፃናት መብቶችን በተመለከተ በዓለም አቀፍ ሕጎች የተደነገገ ቢሆንም፣ የአፍሪካ ሕፃናት የተለየ ችግር ስላለበቸው በተለየ ሁኔታ የአፍሪካ ሕፃናት መብቶችን መደንገግ አስፈላጊ ሆኗል፡፡ ዓለም አቀፉ የሕፃናት መብቶች ድንጋጌ የአፍሪካን ሕፃናት ችግር በበቂ ሁኔታ ሊፈታ የማይችል መሆኑን ለማስረዳት እና ራሱን የቻለ አፍሪካዊ የሕፃናት መብቶች እና ደህንነት ቻርተር መዘጋጀት እንዳለበት ብዙ ምሁራን አሳስበዋል፡፡ በዚህ ረገድ የቀረቡት ምክንያቶች፤

አንደኛ፣ ዓለም አቀፉ የሕፃናት ኮንቬንሽን የአፍሪካን ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ነባራዊ ሁኔታ ያላገናዘበ መሆኑን፣

ሁለተኛ፣ በኮንቬንሽኑ የሕፃናት መብቶችን የሚመለከቱ የአፍሪካ ታሪካዊ እና ባህላዊ እሴቶች አለመካተታቸውን፣

ሦስተኛ፣ ዓለም አቀፍ ሕግ ከአህጉር አቀፍ ሕግ አንፃር ሲታይ በተደጋጋሚ የአፈፃፀም ችግር ስለሚያጋጥመው እና የአህጉር አቀፉ ሕግ ግን ብዙውን ጊዜ ከሕብረተሰቡ ማሕበራዊ እና ባህላዊ እሴቶች ጋር የተቀራረበ በመሆኑ የበለጠ ተቀባይነት እና ይሁንታ የሚኖረው መሆኑን

የሚገልፁ ናቸው፡፡ በዚህም መሠረት እ.ኤ.አ በ1999 የአፍሪካ የሕፃናት መብቶችና ደህንነት ቻርተር ሊፀድቅ ችሏል፡፡

በቻርተሩ አንቀፅ 4 ንዑስ አንቀፅ 1 ላይ በግልፅ እንደተደነገገው ሕፃናትን የሚመለከት ተግባር በማንኛውም ሰው ሲከናወን፣ ይህ ድርጊት ለሕፃናቱ ደህንነት እና ጥቅም ቅድሚያ የሚሰጥ መሆን አለበት፡፡[38] ከድንጋጌው የመጨረሻ ሀረግ እንደምንረዳው ከዓለም አቀፉ የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን በተለየ መልኩ ቻርተሩ ለሕፃናት ጥቅም እና ደህንነት የተሻለ ጥበቃ አድርጓል፡፡ ምክንያቱም ከላይ እንደተጠቀሰው ሕፃናትን የሚመለከቱ ማናቸውም እርምጃዎች ሲወስዱ የሌሎች ሰዎች ጥቅም ከግምት ውሰጥ የሚገባበት አጋጣሚ እንደሚኖር የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን አንቀጽ 3(1) የሚደነግግ ቢሆንም፣ የአፍሪካ የሕፃናት መብቶችና ደህንነት ቻርተር ከዚህ በተለየ መልኩ ሕፃናትን የሚመለከቱ ሥራዎች ሲከወኑ የሕፃናት ደህንነት እና ጥቅም ቅድሚያ እንደሚሰጠው፣ ማለትም በሕፃናቱ መብቶች ፈንታ ሌሎች ጥቅሞችን ማስቀደም እንደማይቻል በግልፅ ደንግጓል፡፡

## 6. ለሕፃናት ጥቅምና ደህንነት ቅድሚያ የመስጠት መርህና አፈፃፀም ከኢትዮጵያ ሕጎች አንፃር

በአገራችን የሕፃናትን ብቃትና ልምድ ማነስ የሚያሳዩ የተለያዩ አሉታዊ ምሳሌዊ አነጋገሮች ይነገራሉ፡፡ ከነዚህም መካከል ‘ልጅ ያቦካው ለራት አይበቃም’፣ ‘የልጅ ነገር ሁለት ፍሬ አንዱ ብስል አንዱ ጥሬ’፣ ‘ከሕፃን አትጫወት ይወጋሃል በእንጨት’ ወዘተ… የሚሉ አባባሎችን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ያም ሆኖ ግን፣ በተለያዩ የኢትዮጵያ ሕጎች ውስጥ ተጨማሪ ጥበቃ ለሕፃናት ተሰጥቷል፡፡

38 “In all actions concerning the child udertaken by any person or authority, the best interests of the child shall be *the primary consideration.”* (Article 4(1) of the African Charter on the Rights and Welfare of the Child 1999.)

ለሕፃናት ጥቅምና ደህንነት ቅድሚያ መስጠት የሚለው መርህ በኢትዮጵያ የተለያዩ ሕጎች ተካቶ የሚገኝ ሲሆን፣ ኢትዮጵያ ያፀደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 9(4) መሠረት የአገሪቱ ሕግ አካል ናቸው፡፡ ስለሆነም በሕገ መንግሥቱ ምዕራፍ 3 ላይ የተዘረዘሩት ሰብዓዊ መብቶች ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ሕግጋት፣ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ስምምነቶች እና ዓለም አቀፍ ሰነዶች መርሆዎች ጋር በተጣጣመ መንገድ መተርጎም እንዳለባቸው የሕገ መንግሥቱ አንቀፅ 13(2) ይገልፃል፡፡ በመሆኑም መርሁ በ1987 ዓ.ም ፀድቆ በወጣው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀፅ 36 ንዑስ አንቀፅ ሁለት መሠረት የሚከተለው ተደንግጓል፡-

> "ሕፃናትን የሚመለከቱ እርምጃዎች በሚወሰዱበት ጊዜ በመንግሥታዊ ወይም በግል የበጎ አድራጎት ተቋሞች፣ በፍርድ ቤቶች፣ በአስተዳደር ባለሥልጣኖች ወይም በሕግ አውጪ አካላት የሕፃናት ደህንነት በቅድሚያ መታሰብ አለበት፡፡"[39]

ከዚህ በተጨማሪ በፌዴራልም ሆነ በክልል የሚገኙ ሕግ አውጪ፣ ሕግ አስፈፃሚና የዳኝነት አካሎች በሕገ መንግሥቱ ሦስተኛ ምዕራፍ (ማለትም ከአንቀጽ 13 እስከ 44) የተደነገጉትን መሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶች የማክበርና የማስከበር ግዴታ ያለባቸው መሆኑ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 13(1) ተደንግጓል፡፡ ይህ ድንጋጌ በተለይ ከአፍሪካ የሕፃናት መብቶች እና ደህንነት ቻርተር ድንጋጌ ጋር የሚጣጣም ነው፡፡

ከሕገ መንግሥቱ ድንጋጌ በተጨማሪ የሕፃናትን መብት እና ጥቅም የሚመለከቱ ጉዳዮች በአገሪቱ የተለያዩ ሕጎች ተካተዋል፡፡ በ1992 ዓ.ም በወጣው የፌዴራል የቤተሰብ ሕግ አንቀፅ 218 እና 312(2) ላይ በግልፅ እንደተደነገገው፣ አካለ መጠን ያልደረሱ ልጆችን የሚመለከቱ ውሳኔዎች ሲሰጡ ለልጆች ደህንነት እና መልካም አስተዳደግ የሚበጁ መሆን እንዳለባቸው ተደንግጓል፡፡ ለምሳሌ የልጅን መልካም አስተዳድግ፣ ፍቺ፣ ትምህርት፣ በአሳዳሪነት እና ሞግዚትነት፤ ቀለብ፤ሞት/መጥፋት ወይም ችሎታ ማጣት፣ ጉዲፈቻ እና አባትነትን ማረጋገጥ ወዘተ ሁኔታዎችን በተመለከተ ውሳኔ ሲሰጥ፣ ውሳኔ ሰጭ አካላት (በተለይ ፍ/ቤቶች) ለሕፃናት ጥቅም እና ደህንነት ቅድሚያ መስጠት እንዳለባቸው የፌዴራል የቤተሰብ ሕጉ በአፅንኦት ይገልፃል፡፡

ለምሳሌ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ በሰበር መዝገብ ቁጥር 35710/2001 (በእፀገነት እሸቱና እና ሰላማዊት ንጉሤ መካከል በነበረው ክርክር) የዚህ መርህ አስፈላጊነት ተገልጧል፡፡ ከዕድሜያቸው ለጋነት በተያያዘ ሕፃናት ለአደጋ የተጋለጡ የሕብረተሰብ አካላት /vulnerable groups/ መሆናቸውንና ሕፃናትን በሚመለከቱ ጉዳዮች ለሕፃናት ጥቅምና ደህንንነት /the best interest of the child/ ቅድሚያ እንደሚያስፈልግ በውሳኔው ተገልጧል:: ከዚህ በተጨማሪ፣ በሰበር መዝገብ ቁጥር 23632/2000 (በፀዳለ ደምሴ እና ክፍሌ ደምሴ መካከል በነበረው ክርክር) ስለሕፃን ብንያም ክፍሌ የአሳዳሪነት እና ሞግዚትነት ጥያቄ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰጠው ውሳኔ ለሕፃናት ጥቅምና ደህንነት ቅድሚያ የመስጠት መርህ እንዴት መተርጎም እንዳለበት በአፅንኦት አብራርቷል፡፡ በዚህ ረገድ የሥር ፍ/ቤቶች ከላይ በጠቀስነው ጉዳይ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ማድረጋቸውን እንደሚከተለው ገልጧል፡-

> "… የክልሉ ፍርድ ቤቶች የሕፃን ብንያም ክፍሌን ሞግዚትነት አስመልክቶ የቀረበላቸውን ጉዳይ ሲመረምሩ ከሕጎቹ ግልጽ ድንጋጌዎች ባሻገር ሕገመንግሥቱ ያስቀመጠውን የሕፃኑን ደህንነትና ጥቅም የማስከበር መርህ ተግባራዊ ማድረግ ሲገባቸው በተለይ የአሁኑ ተጠሪ በዚህ ደረጃ የሞግዚትነት ጥያቄ ያነሣው ሕፃኑ ልጅ «ከእናቱ በውርስ ከሚያገኘው ንብረትና ሀብት ላይ ተካፋይ ለመሆን አስቦ ስለመሆኑ» የከፍተኛው ፍ/ቤት በውሣኔው ላይ ገልጾ ሕፃኑን ከመውለድ ውጭ ከአሥር ዓመታት በላይ ዞር ብሎ ያላየውን፣ ያልተንከባከበውን፣ ያላሳደገውን እንዲሁም ፍላጎቱን እንኳን ያልጠየቁትን ሕፃን በሰላምና በእንክብካቤ ካደገበት ቤት አስወጥቶ በአሁኑ ተጠሪ ሞግዚትነት ሥር ይተዳደር ተብሎ የተደረሰበት መደምደሚያ የሕፃኑን ደህንነትና ጥቅም ያላገናዘበ ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች ከሕጎቹ ግልጽ ቃላት ባሻገር የሕጎቹን ዓላማና መንፈስ በቅጡ ሳያጤኑ የአንቀጾቹን ግርድፍ ቃላት ብቻ በመውሰድ ሕገመንግሥቱን በሚጋፋና የሕፃኑን መብትና ደህንነት በሚጎዳ አኳኋን የሰጡት የሞግዚትነት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ብለናል፡፡"

[39] Article 36(2) of the Federal Democratic Republic of Ehtiopia Constitution 1995

በአንፃሩ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 43988/2003 ሳይፋቱ ተለያይተው ፍቺን በሚያሳይ አኳኋን የሚኖሩ ተጋቢዎች በመካከላቸው የሚታየው የእውነታ ፍቺ/ ሳይፋቱ ፍቺ (*de facto divorce*) ከፍ/ቤት ውጭ ፍቺ እንደተፋቱ እንደሚቆጠር ገልጧል። ይህን የመሰለው ውሳኔ ሕፃናት ለመብት ጥስት እንዳይጋለጡ በር እንዳይከፍት ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ ስላለበት በኤፌዴሪ ሕገ-መንግሥት አንቀፅ 36(2) ላይ የተደነገገውን የሕፃናት ጥቅም እና ደህንነት ቅድሚያ የመስጠት መርህን ከግምት ውስጥ ማስገባት ከፍርድ ቤቶች ይጠበቃል። በተመሳሳይ ሁኔታም፣ በጉዲፈቻ ወቅት ፍርድ ቤቶች ተገቢውን ጥንቃቄ በማድረግ ለሕፃናት ጥቅምና ደህንነት ቅድሚያ ሊሰጡ ይገባል። ለምሳሌ ከሃና ዊሊያም ጉዳይ (*Hana William Case*- Inter-County adoption) እንደምንረዳው የውጭ አገር ዜጎች ለሆኑ ጉዲፈቻ አድራጊዎች ፍ/ቤቱ ጉዲፈቻውን ሲፈቅድ ተገቢውን መረጃ  በመመርመር የጉዲፈቻ ስምምነቱ በጉዲፈቻ ለተሰጠችው ሕፃን ጥቅም እና ደህንነት እንደሚበጅ ማገናዘብ ነበረበት። ጉዲፈቻ የተሰጠችው ሕፃን ሀና ለሞት መዳረጓ የሚያሳየው በዚህ ረገድ ፍርድ ቤቶች ሊያደርጉ የሚገባውን ጥንቃቄ ነው።

በ1996 ዓ.ም ተሻሽሎ በወጣው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ በአንቀፅ 53(1)፣ 117(1)፣ 576 እና በሌሎች አንቀጾች በግልፅ እንደተደነገገው ውሳኔ ሰጭ አካላት በተለይም ፍ/ቤቶች ለሕፃናት መብት እና ደህንነት ልዩ ትኩረት እና ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለባቸው ተገልጧል።  ያም ሆኖ ግን፣ ጽንስ ማስወረድን በሚመለከት በኢፌዴሪ ወንጀል ሕግ የተደነገገው ከሕገ መንግሥቱ ጋር ያለውን መጣጣም ማጤን ያስፈልጋል። በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 551 መሠረት በእርግዝና ወቅት (በተለይ ፅንሱ ከአስገድዶ መደፈር ወይም ከቤተሰብ የተገኘ ከሆነ ወይም ከተፀነስ፣ ፅንሱ ለእናቲቱ ሕይወት አደገኛ ወይም ለጤናዋ ጠንቅ የሚሆን ከሆነ፣ ፅንሱ ሊድን የማይችል ወይም ከባድ የአካል ጉዳት (የዲፎርሚቲ) ችግር ካለበት እንዲሁም እናቲቱ በአካል ካልዳበረች እና የአዕምሮዋ ጤንነት ችግር ካለባት ፅንሱን ማቋረጥ በወንጀል አያስቀጣም። የወንጀል ሕጉ ለእናቲቱ ቅድሚያ እንደሚሰጥ ግልፅ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ የሕገ መንግሥቱ አንቀፅ 36(2) ለሕፃኑ ቅድሚያ የሚሰጥ ነው። በዚህም መሠረት የወንጀል ሕጉ 'ፕሮቾይዝ' (pro-choice) የሚለውን መርህ ሲከተል፣ የሕፃናትን መብት በሚመለከት ሕገ መንግሥቱ ለ'ፕሮላይፍ' (pro-life) አማራጭ የበለጠ ቀረቤታ እንዳለው መገመት ይቻላል። ከሕጎች አሰላለፍ እና ትርጓሜ አንፃር (hierarchy and interpretation of laws) ሕገ መንግሥቱ የበላይ ሕግ መሆኑ በአንቀፅ 9(1) የተደነገገ እንደመሆኑ በዚህ ረገድ ተገቢው የአተረጓጎም ጥንቃቄ ከፍርድ ቤቶች ይጠበቃል።

ፍርድ ቤቶች በጋብቻ መፍረስ ረገድ የሚሰጡት ውሳኔም ከሕፃናት መብትና ጥቅም ጋር ተያያዥነት አለው። የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 14290 በወ/ሮ አበበች የሽዋሉል እና በእነ ወ/ሮ እታገኘሁ አድማሱ ክርክር መጋቢት 25 ቀን 1999 ዓ.ም. በዋለው ችሎት "የተጋቢዎች ተለያይቶ ለረዥም ጊዜ መኖርና በዚህም ጊዜ ሌላ ትዳር መሥርቶ መገኘት በእውነታ ፍቺ መኖሩን (*de facto divorce*) አመላካች ስለመሆኑ፣ በሕጋዊ መንገድ ስላልተለያዩ ግንኙነቱ ሕጋዊ ውጤት ሊያስከትል ይቻላል ሊያስብል የሚችል ስላለመሆኑ" ውሳኔ ሰጥቷል። ይህ ውሳኔ በአዋጅ ቁጥር 454/1997 በአንቀጽ ቁጥር 2 ንኡስ አንቀጽ 1 መሠረት *በየትኛውም ደረጃ ላይ የሚገኙ የፌዴራል ወይም የክልል ፍርድ ቤቶች* ላይ አስገዳጅነት ይኖረዋል። ከርትዕ አኳያ የእውነታ ፍቺ የጋራ ንብረት ውጤትን ያስቀራል ቢባልም ውሳኔው የልጆችን ጥቅምና ደህንነት የማስከበር ጉዳይ ከግምት ውስጥ አላስገባም። ፍቺ በፍርድ ቤቶች ብቻ እንዲወሰን የተደረገበት ምክንያት ፍርድ ቤቶች በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 13(1) የተሰጣቸውን ኃላፊነትና ግዴታ እንዲወጡ ለማስቻል ነው። ከዚህ አኳያም፣ ሰበር ሰሚ ችሎቱ የሚሰጠው ውሳኔ ሕፃናትን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ (ማለትም፣ በጉዲፈቻ ወቅት፣ በወላጆች መለያየትና ፍቺን ተከትሎ ከየትኛው ወላጅ ጋር ማደግ እንደአለባቸው ውሰኔ ሲሰጥ እና በመሳሰሉት ጉዳዮች) ለሕጻናት ጥቅምና ደህንነት ቅድሚያ መስጠት ይጠበቅበታል።

በዚህ ረገድ የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች የሕፃናትን ጥቅምና ደህንነት የማስጠበቅ መርህ ለመወሰን የሚያስችሉ የመገምገሚያ መስፈርት የላቸውም። ይህም የሚያሳየው ፍርድ ቤቶቹ በዚህ መርህ ግልጸኝነት እና አሠራር ረገድ ክፍተት የሚታይባቸው መሆኑን ነው። ስለሆነም፣ ፍርድ ቤቶች የተለያዩ ሕግ-ነክ ጉዳዮችን ሲወስኑ የሕፃናትን ጥቅም በሚጎዳ መልኩ ውሳኔ እንዳያስተላልፉ ጥንቃቄ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

## ማጠቃለያ

ለሕፃናት ጥቅም እና ደህንነት ቅድሚያ መስጠት የሚለው መርህ በራሱ የሕፃናት መብት ከመሆኑ ባሻገር፣ ለሌሎች የሕፃናት መብቶች መፈፀም እና መከበር ትልቅ ድርሻ አለው፡፡ ይህ መርህ በተለያዩ ዓለም አቀፍ፣ አህጉር አቀፍ እንዲሁም አገራዊ ሕጎች ላይ የተለየ እውቅና እና ቦታ ይዞ ይገኛል፡፡ ከዚህም በመነጨ ፍርድ ቤቶች ያላቸውን የሙያ ግዴታና የተሰጣቸውን ሥልጣን መሠረት በማድረግ ለዚህ መርህ መፈፀም እና መከበር የተለየ ኃላፊነት፣ ግዴታ እና ሚና እንዲኖራቸው ተደርጓል፡፡ የሕፃናትን መብቶች በተመለከተ በማናቸውም ጉዳይ ላይ ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሲሰጡ *ለሕፃናት ጥቅምና ደህንነት ቅድሚያ የመስጠትን መርህ* በአንክሮ እንዲገነዘቡ በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥትና በዓለም አቀፍ ሕጎች ኃላፊነት እና ግዴታ ተጥሎባቸዋል፡፡ ስለሆነም፣ ፍርድ ቤቶች በሕፃናት ጉዳይ ላይ ውሳኔ ሲሰጡ፣ ዓለም አቀፍ ሕጎችንና የተለያዩ አገሮችን ልምድ በማጤን፣ ከሕፃናት መብት አንፃር ጉዳዮችን ማየት ይችሉ ዘንድ ለዚህ መርህ መፈጸም ግብአት ሊሆኑ የሚችሉ መመዘኛዎችን ማውጣት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ■

MIZAN LAW REVIEW

ST. MARY'S UNIVERSITY

## Cultural Problems in Research and Publications

Source:
Reform Document on Legal Education and Training in Ethiopia (2006) § 2.4.1/A

1. Lack of research, reading, and writing culture
   - Complacence with our work merely as teachers.
   - No sense of urgency about the need to engage in research and turn up research products.
   - No '*publish or perish*' attitude.
   - No attempt to work beyond the positive laws.
2. Lack of Institutional Commitment
   - In terms of budget, time, and resource allocation for R&P
   - In terms of reduction of teaching load or granting (Research Leave).
3. Lack of team spirit for Research and Publications
   - Among staff members;
   - Between staff and students;
   - Lack of collaboration among institutions.
4. Lack of innovation in diversification of publications, and problems regarding spheres of focus in research.
5. Raising the stakes too high in assessing the quality of publishable manuscripts (despite) shortage of (such) manuscripts.
6. Lack of tradition of salvaging "distressed" manuscripts through sympathetic editing without compromising quality.
7. Weak consumption of research products in the legal professional community and in government institutions, and poor state of constructive feedback.
8. Inadequate attention to relevance of research to the real life or actual problems of the society.

## *Vision of law schools*

**Law schools shall have vision towards elevating the standard and quality of legal education to the level of leading law schools in other countries, and towards preparing graduates who will have optimum impact in Ethiopia's development, democracy, good governance and social justice.**

---

## *Mission of law schools*

**Law schools shall promote the intellectual and social conditions of Ethiopia by providing equitably accessible quality legal education and training programs through teaching, research and service to prepare competent and responsible members of the legal profession who actively contribute towards rule of law, democracy, human rights, good governance, social justice, equality, tolerance and development.**

***Source:*** **Ethiopian Legal Education and Training Reform Document (June 2006)**

*Address*:

**Mizan Law Review**
**St. Mary's University**
**Center for Law in Sustainable Development**
**P. O. Box: 1211 (or 18490), Addis Ababa, Ethiopia**
"We plan each issue as if it were a new book."

**St. Mary's University Press**